የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ጥር ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 11
ADDIS ABABA 21st January, 2020

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፷፩/፳፻፲፪ ዓ.ም
የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ……………………………ገጽ ፲፪ሺ፺፪

Content

Regulation No. 461/2020
Council of Ministers Commercial Registration and Licensing (Amendment) Regulation ….Page 12092

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፩/፳፻፲፪

### የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፪/፳፻፰ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹/፳፻፲ አንቀጽ ፶፪(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክርቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፬፻፷፩/፳፻፲፪” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ማሻሻያ**

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብ ቁጥር ፫፻፺፪/፳፻፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል:-

“፬/ በንግድ ማኅበር የንግድ ስም እንዲሻሻል ሲጠየቅ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ስለመሻሻሉ ለዚህ በተዘጋጀ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታርን በመጠቀም ያሳውቃል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 461/2020

### COMMERCIAL REGISTRATION AND LICENSING (AMENDMENT) REGULATION

**WHEREAS,** it has been found necessary to Amend, the commercial Registration and licensing service Regulation No 392/2016;

**NOWTHEREFORE,** the Council of Ministers has hereby issued this Regulation pursuant to Article 52 (1) of the Commercial Registration and Licensing Proclamation No. 980/2016.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Council of Ministers Commercial Registration and Licensing (Amendment) Regulation No. 461 /2020."

**2. Amendment**

Commercial Registration and Licensing Regulation No.392/2016 is hereby amended as follows:

1/ Sub Article (4) of Article 7 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub Article (4):

"4/ Where a request is made for an amendment of a company name of a business organization, authenticated minutes the relevant organ shall notify the amendment via information communication technology channels.

፪/ በደንቡ በየትኛውም ቦታ ላይ "አመልካቹ የዋና ሥራ አድራሻና የቅርንጫፍ የሥራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንኑ የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ" የሚለው ተሰርዞ "አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ" በሚል ተተክቷል፡፡

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ረ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ረ) ተተክቷል:-

"ረ/ አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሁም ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የንግድ ሥራ አድራሻ የአመልካቹ የንግድ ሥራ አድራሻው ነው ተብሎ ይወሰዳል፡"

፬/ የደንቡ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡

"፪/ ግለሰብ ነጋዴ በውክልና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ለማውጣት ሲፈልግ ወኪሉ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የውክልና ማስረጃ ሠነድ ማቅረብ አለበት፡"

፭/ የደንቡ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሠ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሠ) ተተክቷል:-

"ሠ) ለበጀት ዓመቱ ለደመወዝ እና ለሥራ ማስኪያጃ የሚሆን ቢያንስ ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺ) የአሜሪካን ዶላር ወደ አገር ውስጥ በወካዩ ስም ወይም በእንደራሴው ስም ለማስገባቱ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፡"

፮/ የደንቡ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል:-

"፬/ ማሻሻያው የሚደረገው በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከሆነ የማኅበሩ አባላት ማሻሻያ ያደረጉበትን ሠነድ ለማረጋገጥ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ፡ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ ሠነድን ለማረጋገጥ

2/ The expression which provides "statement of principal business address of applicant and branch office, if any in any of the provisions in the Regulation is deleted and replaced by "the business address stated and signed by the applicant in the form prepared by the relevant body for this purpose."

3/ Paragraph (f) Sub Article (1) of Article 9 of the Regulation is deleted and replaced by the following new paragraph (f):

"f/ Where the applicant is a foreign national, in addition to those provided in this Article, he shall produce an investment license and the business address stated and signed in the form prepared for the purpose by the relevant body shall be taken as his business address."

4/ Sub Article (2) of Article 9 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub Article (2):

"2/ Where a commercial registration of a sole business is made via an agent through a power of attorney, a power of attorney authenticated by a legally authorized body shall be produced."

5/ Paragraph (e) Sub Article (1) of Article 13 of the Regulation is deleted and replaced by the following new paragraph (e):

"e/ a bank statement certifying deposit of a minimum of USD 100,000(One hundred thousand) earmarked for salary and administrative expenses is deposited in the name of the principal or in the name of his representative;"

6/ Sub Articles (4) of Article 18 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub Articles (4):

"4/ The business address stated and signed by the business organization in the form shall be taken as his business address , Where the amendment is to be made to the memorandum or Articles of association, an original copy of the minutes of shareholders decision to amend same, authenticated by a legally